# “የጋዜጠኛው ማስታወሻ ትችት” አስተያየት

አንዳንዴም ነገርን በበጎ መመልከት ጥሩ ይመስለኛል። እኔ በኔ በኩል፣ ይህንን መጽሀፍ በበጎ ተመልክቼዋለሁ። “ተስፋዬ ገብረአብ እስከአሁን የትነበርክ?” በሚል ርዕስ “የጋዜጠኛው ማስታወሻ” ለሚለው መጽሀፍ የተጻፈውን ትችትም ሆነ መጽሀፉን አንብቤዋለሁ። እኔም ትንሽ አስተያየት ቢጤ ሀሳቤን ወርወር ላድርግ አሰኘኝ። እናም በመጀመሪያ በኔ አስተያየት ትችቱ “ቅንነቱ” አነስ ያለ መሰለኝ (ግላዊ አስተያየቴ መሆኑም ይሰመርበት)። እዚህ ላይ ነገሮችን በንጽጽር ብንመለከት ጥሩ ነው። ብዙዎች ውስጣቸው ታፍኖ፣ መተንፈሻ ያጡ መኖራቸውንም ከግንዛቤ እንክተት። የዚህ አስተያየት ጸሃፊ የመጽሃፉን ደራሲ በአስተያየታቸው፣ “እዚህ ጋ ደራሲው ይህንን ጥሩ ብለዋል” ያሉበት ቦታ ጎልቶ አይስተዋልም።

ሌላው፣ አብዛኞቻችን (... አብዛኞቻችን ከምናውቀው ውጭ ይኽ ነው የሚባል ቁም ነገር የለም።) እና ማንም እንደሚያውቀው (እንትና የተገደለው በእንትና እና በእንትና ስራ እንደሆነ ማንም እያወቀው...) የሚሉት አይነት ማጠቃለያዎች ጥናትን የተንተራሰ ስለማይመስለኝ ቁጥሩን አሻሚ ያደርገዋል። ስለዚህ ወይ በመረጃ እንደግፈው አለበለዚያ በዚህ መልኩ ባናጠቃልለው።

የአንዳንድ ክስተቶች አለመጠቀስ ... እንትና እና እንትናን ተችቶ የጻፈበት ቦታ የለም... እንደትችት ተጠቅሷል። በርግጥ ነው፣ ቢካተቱ ኖሮ ተብሎ በአስተያየት መልክ ቢቀርብ ገንቢነቱ ይታየኛል። ምክንያቱም ባለብዙ መድብሉ ኢንሳክሎፒዲያ እንኳን ሁሉን ነገር አያካትትምና። ባይሆን በቀጣዩ መጣጥፋቸው ወርወር ሊያደርጉት ስለሚችሉ።

የእርስዎ አቋም ፀረ-ኢህአዲግ (ፀረ-ወያኔ) ከሆነ እኔ እርስዎን ብሆን ኖሮ፣ ወያኔ (አመራረ-መለስ) ካሰለፋቸው በርካታ ጀሌዎች ከዋናዎቹ አንዱ በመወገዱ በራሱ አንድ ስኬት ነው እል ነበር። ሌላው ደግሞ፣ በየትኛውም መመዘኛ፣ ትልቅ የሆነ የወያኔ ምስጢር (ከትልቁ አፋቸው በአንዱ) አደባባይ ውሏል። ነው ወይንስ እንደ አቶ ታምራት ላይኔ በ “በልቻለው ሆዴ” መቋጨት ነበረበት። ይልቅ “ከፈረሱ አፍ” ይሉት አይነት ከምንጩ ነገሩ ይፋ መሆኑ ጥሩ ነው እላለሁ። በነበር በቃ የተተረከ ሳይሆን፣ የአሁንም አለ መንፈስ ስላለው፣ በትልቁ እውነትን ለማሳየት ያስችላል። ይልቅስ ወያኔን ለዚህ ምን ትላለህ ማለቱ ነው የሚበጀው።

መለስ ዜናዊ ለምን “ብልህ” ብሎ አወደሳቸው ይላል በጽሁፍዎ። ምናልባት “ተንኮለኛ” ለምን አልተባለም ካልሆነ በስተቀር፣ ስንቱን መንጋ ጀሌ በ “እሺ ጌታዬ” አቀባበል መነተታቸው ይህንን ስም አያሰጣቸውም ይላሉ? እንደ ደርግ ያሳደጉትን ውሻ በጥይት አይሉም። ባይሆን ያስሩታል ወይም እራሱን እንዲያባርር ያደርጉታል እንጂ። መረጃ ባይኖረኝም፣ ለቅንጅት እዚህ መድረስ እጃቸው አይኖርበትም ይላሉ? እኔ በበኩሌ ምናለ ይህንን ጭንቅላታቸውን ለበጎ ባዋሉት የሚያሰኙ አይነት ናቸው የሚል ግምት አለኝ።

ብዙ ማተቴን ገታ ላድርግና ለዚህ መጫጭሬ ማዕከል ወደሆነው ሀሳብ ልመለስ። ውስጥ ያሉትንም፣ የከዱትንም፣ በመስመሩ ስህተትነት አምነው ከህዝብ የተቀላቀሉትንም “ወግድ” ካልን፣ በምን አካሄድ ጀሌዎችን መቀነስ ይቻላል። ከአህያ የዋለች... በሚሉት አይነት ካልደመደምነው በስተቀር፣ በተለይ በዚህ ወቅት፣ እገምታለሁ፣ አብዛኛው ጀሌ ለጥቅም (ለመኖር) ሲል ከማድረግ ባሻገር የጠለቀ የድርጅታዊ አለኝታነት ስሜት የለውም እላለሁ። ስለዚህ፣ ይህ አጋጣሚ ለሌሎች ጀሌዎች የይቅርታ መጠየቂያ ግዚያቸው ከማለፉ በፊት ይቅርታ ለመጠየቅ በሩን ስለሚከፍት በቀና መቀበሉ ጠቀሜታው የጎላ ነው። ያም ወያኔን የበለጠ እርቃኑን እንዲቀር ያደርገዋል። ውጤቱም ከቻለ ፈጣን የሆኑ ማስተካከያዎችን ወስዶ ለሰላማዊ እና አገራዊ የውይይት አጀንዳዎች መንገዱን ይጠርጋል። ካልሆነም ለሌላኛው አማራጭ፣ በምርጫ ስልጣንን ለማስተላለፍ ከቃል ባለፈ በተግባር የተደገፈ ለመጪው ምርጫ ዲሞክራሲያዊ ተቋማትን እንዲገነባና ያሉ የሚመስሉትንም እንዲያጠናክር ይገደዳል። የዚህም አጠቃላይ ውጤቱ፣ በአንድ ወቅት ተስተውሎ የነበረውና ወዲያውኑ የከሰመውን፣ የህዝብን የራስን ተወካይ ለህዝብ ባለአደራነት ለማምጣት የሚያስችለውን መንፈስ ይመልሳል። ከዚያም የማይታመን መስሎ ግን ዕውን የሆነውን “ጥቁር” ለዓለም የነገሰበትን አይነት ዲሞክራሲ በቅርብ ርቀት እንድናልመው ያስችለናል።

ሰው አጥታ ነው እንጂ ያች ምድር
እንደ መጀመሯ የት ደርሳልን ነበር።

ከላቀ ምስጋና ጋር!

ብራቫሌክ ነኝ

ከአገረ እንግሊዝ